# እኔም ስለ ዶ/ ብርሀኑ ትንሽ ልበል      ከእለኔ አለሙ

ዶ/ ር ብርሀኑ ነጋ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ሊቀመንበር  የአርበኞችን ትግል ስለመቀላቀላቸውና ትግሉ የደረሰበት ደረጃ የአመራሩ የቅርብ እገዛ በማስፈለጉ እርሳቸውና ከፍተኛው አመራር አስመራ መግባታቸው  በእሳት ራዲዮና ቴሌብጅን ከተነገረ ጀምሮ ስለ ዶክተር ብርሀኑ የፖለቲካ ተክለ ሰውነት ስለ ቆራጥ አመራራቸው ፣ ችሎታቸው ና ፅናታቸው  በየ ድረ- ገጾች ፣ሚዴያዎችና ፖል ቶክ ብዙ ስለተባለና ስለ ተፃፈ እኔም የማውቀውን እውነተኛውን ነገር ለማካፈል ብእሪን አነሳሁ ።

ከሁሉ በፊት በአሁኑ ጊዜ የዶክተር ብርሀኑ ነጋ ታሪክ አምሮና ገዝፎ እንዲነገር የሚፈልጉ ክፍሎች እነማን ናቸው? ይህ ቡድን ከላይ ሁኖ የሚመራው ማነ ነወ? የዚህ ቡድን ዓላማና ግብ ምንድነው? የሚሉትን ጉዳዩች ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

ዶ/ ር ብርሀኑ የመድረክ ሰው ነው ። ሕዝብን የሚወደውንና የሚፈልገውን ነገር ምሁራዊ በሆነ ቋንቋ በመናገር ሕዝብን  የማስደሰት ችሎታ አለው። በስብሰባ ሕዝብ  ካስደሰተለት ነገ እጠየቅበታለሁ ብሎ  ኃላፊነት የጎደለው ንግግር በማድረግ  እንደ ዶ/ ር ብርሃኑ  የሚታወቅ የለም። ዶ/ ር ብርሀኑ ባለፍት ሀያ አምስት ዓመት በተደረገው የዲሞክራ
ሲ ና የነፃነት  የሕዝብ ትግል ካበረከተው አስተዋጽኦ ይልቅ የሰራው በደል፣ አሻጥርና ክህደት ይበልጣል።ነገር ግን  ዶ/ ር ብርሀኑን ከፖለቲካ  መድረክ አሁንም በመሪ ተወናይነት እንዲቀጥል  ያስቻሉት የተደራጀ ሁለት ማህበራዊ መሰረት አሉት ።እነርሱም  አንደኛ ዶ/ ር  ብርሀኑ የተወለደበት ማህብረሰብ ታታሪና ሰራተኛ ብቻ ሳይሆን ተባባራና ደገፊ ጭምር ነው። የዶክተሩ አባት ከአንስተኛ ሥራ  ተነስተው በላባቸውና በጉልበታቸው ከፍ ካለ ደረጃ ደርሰው ሌሎች ወገናቸውን መርዳታቸው  በጉራጌው ብሔረሰብ አባትየውና ቤተሰቡን አንደ ተምሳሌት ይወሰዳሉ የጉራጌ ማህብረተሰብ በባህሉ መረዳዳትና መደራጀት ያውቃል አሁን በስልጣን ያለው የህዋት አስተዳደር መንግሥት ደግሞ የሥልጣን መሰረቱ ብሔርተኝነት ነው ይህ አካሄድ ደግሞ ይህን

ማህብረተሰብ ይበልጥ ክልላዊ ያደርገዋል ፡፡ከሁሉ በላይ የህዋት መራሹ የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት በዘርና በደሙ ተደራጅቶ በሌላው ኢትዮጵያዊ ጥቃት እንዳደረሰው ሁሉ የጉራጌው ማህብረተሰብ በዚህ ዘረኛና አምባገነን መንግሥት ሰለባ ሁኖአል አብዛኛውን የጉራጌውን ማህብረተሰብ ከንግድና ከአገልግሎቱና ከአትራፊ ንግድ ሥራዎች ዉጭ በማድረግ የተጋፋ ና የተገለለ ማህብረተሰብ ነው ፡፡ይህ የጉራጌ ማህረተሰብ እንደ ሕዝብ ከፖለቲካና ከአስተዳደር ተሳትፎና ሥራ ይልቅ በንግድና በአገልግሎት ሥራና ተሳትፎ የነበረው የጉራጌው ማህብረተሰብ በገዥው
የህዋት አምባገነን መንግስት በደረሰበት በደልና ግፍ ሥርዓቱን ለመታገል የመነቃቃትና ሥርዓቱን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል እንደ ሌላው ዜጋ የተነሳበት ወቅት ነው ፡፡ ዶ/ ር ብርሀኑ ይህን ራሳቸው የተወለዱበትን ማህብረተሰብ ያለበትን ደረጃ ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ አንዳንድ የዚህ ማህብረተሰብ አባላት የሆኑት ስብስቦች ዶ/ ር ብርሀኑ የጉራጌ ብሔረሰብ በመሆኑ ብቻ በተደራጀ መልኩ በጭፍን ከነ ድክመቱና ችግሩ ይደግፍታል፡፡ ከሺ ያልተደራጀ ኃይል አምስት የተደራጀ ቡድን የበለጠ ጉልበት አለው፡፡ ዶ/ ር ብርሀኑ ይህ የተደራጀ ቡድን ባይኖር ኑሮ ቢያንስ በምርጫ 97 የኢትዩጵያ ህዝብ ድምፅን ለማስከበር የተዘጋጀበትን አመጽና አድማ ከገዥው መደብና ከአሜሪካ ጋር ባደረጉት ስምምነት ማክሸፋቸው ፣ ጠንካራ ተፎካካሪ የነበረውን የቅንጅት ፓርቲን ለማፍረስ የቅንጅትን አመራሮች በዚሁ አጋሮቻቸው አመካይነት ስም በማጥፋት ትግሉን ለማኳላሸት የሄድበት የተደራጀ አካሄድ ሲታሰብና በሀገር ቤት ያሉ ሰላማዊ ትግል የሚካሄድ የፖለታካ ድርጅቶችን ለማዳከምና ደብዛቸውን ለማጥፋት በተጨማሪም በውጭ ሀገር ደጋፌ ኮሚቴዎቻቸዉን እንዴት እንዳፈረሶቸው ሲታይ ዶ/ ር ብርሀኑ ነጋ በኢትዩጵያ በመሪነት ደረጃ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን በሚኖርበት አካባቤ መታየት የሌለባቸው ግለሰብ በሆኑ ነበር፡፡ ባለፍት ሀያ አራት ዓመት በኢትዩጵያ ፖለቲካ አዎንታዊና አሉታዊ ተጹእኖ ፈጣሪ የነበሩ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች ደብዛቸው የጠፋ ህዋት ኢህአዴግ በፈጠረው አፈናና የኃይል እርምጃ ብቻ ሳይሆን ዶ/ ር ብርሀኑና ተከታዮቻቸው ባደረጉት ቅስቀሳና የስም ማጥፋት ዘመቻ ጭምር

ነው። አነ ልደቱ አያሌው ፣ እንጅነር ኃይሉ ሻውል፣ ዶ/ ር ታዬ ወልደሰማያት፣ በአጠቃላይ በሀገር ቤትና በውጭ ሀገር በግንባር ቀደምነት መሪና አክትባስት የነበሩ ጥቃት የተሰነዘረባቸው በዚሁ በዶ/ ር ብርሀኑ በሚመራ የጋንግ ስተር ቡድን ነው። ከላይ ስማቸው  የተዘረዘረው ና ሌሎችንም ታዋቃ ፖለቲከኞችና የሙብት ተማጓኞች ደብዛቸውን የጠፋው  በዚህ ቡድን አመካይነት ነው ። እነዚህ ከፖለቲካው መድረክ የተገፍ ኃይሎች አጥፍተዋል የሚባል ጥፋት ቢኖር እነኳ ዶ/ ር ብርሀኑ በሕዝብ  ትግል  ከሰራው  ሴራና ተንኳል አንፃር ሲነፃፀር  ሚዛን ላይ የሚቀመጥ አይደለም ልይነቱ ዶ /  ር ብርሀኑ ነጋ እሱነቱን የሚጠብቁና የሚከላከሉ  ከመሪት አንስተው ሰማይ የሚደርሱ ሰብእና የጎደላቸው እውቀት የለላቸው ተናዳፊዎችና ተሳዳቢዎችን በማደራጀቱ ብቻ ነው ዶ/ ር  ብርሀኑ አሁንም በኢትዮጵያ ፖለታካ መቆየት የቻለው

ሁለተኛው የዶ/ ር ብርሀኑና የድርጁታቸው የድጋፍ ማህበራዊ መሰረታቸው ከአቢሲኒያ ቅኝ አገዛዝ  ነፃ መዉጣት አለብን የሚሉ ነፃ አውጭዎችና የሻቢያ ድርጅት ናቸው። ሻቢያ ግንቦት ሰባት የተባለው ድርጅትና መሪው ዶ/ ር ብርሀኑ የነበረባቸውን የፖሊቲካ አጣብቂኝ በደንብ ያውቃሉ። ከቅንጁት አመራሮች ከእስር መፈታት ማግስት በፍርሀቱና በደንጋጠነቱ የሚታወቀው ዶ/ ር ብርሀኑ ነጋ  ሀገር ቤት  በመመለስ ትግሉን በመቀላቀል ከሥርዓቱ ጋር ለመጋፈጥ ወኔና ቁርጠኝነት በማጣቱ በዉጭም ሀገር ለመቅረቱ ለራሱና ለተከታዮቹ የሞራል ክብር ለመስጠትና በዲያስፖራው የሚገኘውን ትግል ለመከፋፈል ሁለገብ ትግል አደርጋለሁ በሚል ግንቦት ሰባት የተባለ ድርጅት አቆቁሚለሁ በሚል አወጀ። ያለውን የህዋት አገዛዝ በሁለተናዊ  ትግል አንበረከካለሁ ያለው ግንቦት ሰባት ድርጅት ፕሮግራሙን ሲውጁ  ወታደርና ይህን ሥራ  ለመስራትና ለመጀመር አንድም ድርጅታዊ መዋቅር አልነበረውም። ግብና አላማ አድርጎ የተነሳው ነፍጥ ያነሱትን ነፃ አውጭ ድርጅቶችን ነው በተለይ  የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት፣ የኦጋዴን ፣ ትብዲን፣ የአፋርና የደቡብ ሕዝቦች ንቅናቄ ና በተለይም የኤርትራ መንግሥት ( ሻቢያ) ነው ። እነዚህ ነጻ አውጭዎች ኢትዮጵያ በምትባል ሀገር ቅኝ ለሙቶ አመት ተገዝተናል አሁን በስልጣን ያለው አገዛዝ  ካለፍት ስርዓቶች ሲነፃፀር

ብዙ የዲሞክራሲ መብታችን ያስከበረ ቢሆንም ዋነኛውን የትግላችን መሰረት የሆነውን ከአብሲንያ ነፃነታችን ማግኘትና ማረጋገጥ የሚለውን ለድል ለማብቃት ነው።ህዋት ኢህአደግ ደግሞ በህገ መንግሥቱ  የደነገውን አንቀፅ 39 ተግባራዊ አላደረገም ይህን ተግባራዊ ማደረግ የሚችለው ወያኔ ሲገደዱና ሲወጠር ብቻ ነው ለዚህ ብረት አንስተን  እየታገልን ነው ይህን ዓላማችንና መርሆችን ከሚቀበልና ከሚከብር ማንኛውም ኃይል ጋር አብረን እንሰራለን የሚል ነው ። ግንቦት ሰባት በባዶ እጅ በቀቢፄ ተስፋ የጀመረው የወረቀት ትግል የሚረግጠዉ መሪት የሚሸሽግበት ታዛ በማጣቱ ትግሉን ከፊት ሁኖ የሚመራበትን እድል ትቶ የሌሎች ነፃ አውጭ ድርጅቶችና የሻቢያ ጉዳይ አስፈፃሚና ተላላኪ መሆን ብቻ አማራጭ ሆነ። ብርሃኑ ነጋ ግንቦት ሰባትን ሲቋቁም ታሳቢ አዱርጓ ለወደፊት አጋዥና አጋር አድርጓ ያሰባቸው  ሻቢያ፣ ኦነግ፣ የኦጋዴን ነፃ አውጭ ድርጅት፤ትህዲን፣የደቡብ ሕዝቦች ዲሞክራሲ ንቅናቄ ፣የአፋርና የሱማሌ ነፃ አውጭለሌሎች በማሰብ  ነው ። ዶ / ር ብርሃኑ ከሻቢያና ከነፃ አውጭ ድርጅቶች በተለይ ከኦነግ ቢያንስ የተላላኪነት ሚና ለመጫወትና እኛም በጦርነቱ ፍላሚያ አለን ለማለት ርካሽየፖለቲ ፍጆታ ለማግኘትና ህዝብን በማወናበድ ገንዘብ ለማግበስበስ ከጅምሩ ግንቦት ሰባት ሲቋቋም ቢያንስ በሻቢያና ኦነግ አዎንታዊ ተቀባይነት ለማግኘት  ሁለት ዜዴዎችን ተጠቀመ

አንደኛው  ሻቢያ፣ኦነግና ሌሎችም ነፃ አውጭ ድርጅቶች የማይወድት ይልቁን አምርረው የሚታገሉትን  በአንድነት ኃይሎችና ኢትዮጵያዊነትን በሚቀነቅኑ ኃይሎች ላይ ከበድ የማጥላላትና የማፍረስ ስራ በመስራት ለሻቢያና ለኦነግ ያለውን ፍቅር ለመግለፅና ለማሳየት  ዶ/ ር ብርሀኑና ዱርጅታቸው  በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ በተለይም ሻቢያናኦነግ ጠላትና መጥፋት አለበት ብለው ከፍተኛ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሲደርጉበት በነበረው በአማራው ብሔር ላይ ከፍተኛ  ጥቃትና የመጥላላት ዘመቻ በማድረግ የዓላማ አንድነታቸውና ድጋፋቸውን አሳይተዋል ።

ሁለተኛው ግንቦት ሰባት ለሻቢያ፣ ለኦነግና ለሌሎች ነጻ አውጭዎች ያለውን ተአማኝነት ለማረጋገጥ ድርጅቱ ሲዋቀር  ከአማራ ጽንፈኞችና

አንድነትን ከሚቀነቅኑ ኃይሎች የፀዳ ነው በሚል ኢትዮጵያዊያንን ሆን ብሎ በማግለል ግንቦት ሰባት ድርጅት በራሱ የነፃነት ድርጅቶች የህብረት ግንባር በሚመስል የተቋቋመ ድርጅት ነው ። የግንቦት  ሰባት ከከፍተኛ አመራር እስከ መካከለኛና አንስተኛ አመራር ያሉትን ብንመለከት በአንድ ኢትዬጵያ ላይ ችግር ያለባቸው ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ውስጣቸውና ልባቸው ከነጻ አውጭዎች ጋር  ያበረ ግለሰቦችን ያሰባሰበ በአጠቃላይ ግንቦት ሰባት ከአብስኒያ( ከኢትዮጵያ ) ቅኝ ግዛት ነፃ እንወጣለን ከሚሉ ራሳቸውን ነፃ አውጭ ድርጅት ብለው የሰየሙ ድርጅቶች የነርሱ የጥምረት ድርጅት ነው። ግንቦት ሰባት በሁለተኛ ረድፍ በመሰለፍ ሻባያና ኦነግ ይህችን  ሀገር ከዘጠኝ ለመበተን በሚደረገው ደባና ሴራ በቅጥረኝነትና በተላላኪነት እየሰራ ነው። በግንቦት  ሰባት ድርጅት አመራር ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው እነዚህ ነፃ አውጭዎች ብቻ ሳይሆኑ የሻቢያ ወኪል የሆኑ ኤርትራዊያንም ድርጅቱን በመምራትና  በማደራጀት ከፍተኛ ሚና አላቸው ።

በአጠቃላይ በሻቢያ አስተባባሪነት የሁሉም ነፃ አወጭ ድርጅቶች በፕሮፖጋንዳ ተግባር በዶ/  ር ብርሀኑ ነጋ ከሚመራው ድርጅት ከግንቦት ሰባትና ከድርጅቱ ልሳን ከእሳት ራዲዬና ቴሌብዥን ጋር አብረው በጥምረት እየሰሩ ነው። ዋነኛው ግባቸው ከህዋት ወያኔ ይልቅ ኢትዩጵያዊ የአድነት ኃይሉን ማዳከምና ማንበርከክ ነው በተጨማሪ  ሻባያና መሪው ኢሣያስ አፈወርቂ የሀገራችንን እጣ ፈንታ ወሳይ መሆናቸውን ፕሮፖጋዳ ማድረግ ነው። ለዚህ ተግባራቸው ሻቢያ፣ኦነግ፣የደቡብ  ህዝቦች ዲሞክራሲ ንቅናቄ ፣ የኦጋዴንና የሶማሌ ነፃ አውጭ ድርጅት አማርኛ የሚናገሩ ካድሬዎቻቸው የግንቦት ሰባትና የአርበኞች ደጋፊና አባል በመምሰል በኢትዮጵያዊ አድነት ኃይል ከፍተኛ ጦርነት ከፍተዋል ። እነዚህ ኃይሎች ኢትዬጵያዊ የሆነ ባህልና ግብረገብነት ስለሌላቸው ሰውን በሀሳብ የበላይነት ሳይሆን በስድብና በጋጠወጥ ንግግር አንገት ማስደፋት ይጥራሉ ። ጨዋና ባለጌ ቢፎካከሩ ባለጌ ሁሌ አቸናፊ የሆነ ይመስለዋል። ከዚህ በተጨማሪ የኢትይጵያ አንድነት በነ ብርሀኑ ነጋ ይመጣል በሚል በጭፍን የሚደግፋቸው ኢትዮጵያዊ  አንድም ምንእያደረጉ እንደሆነ ያልተረዱ ነገር በደፈናው የሀገርና የነፃነት ጥማት

ያላቸው የሚመስሉ ድንግል መሃይም ስለሆኑ ስለ እነርሱ አስተያየት መስጠቱ ጠቁሚ አይደለም አይጠቅምም። ኢትዮጵያን ለማፍረስ እየተባበሩ እንደሆነ በታሪክም ተጠያቂ እንደሆኑ እንዲውቁት እፈልጋለሁ ።

የፅሑፉ ርዕሰ እኔም ስለ ዶ/ ር ብርሀኑ የምለው አለኝ የሚል ነው ተያያዥ ጉዳዩች ላይ አተኳርኩ ብርሀኑ ነጋ ሁለት የማይለቁ ባህሪት አሉት አንደኛው ክህደት ነዉ በቅርብ ለሩብ ምእተ አመት አውቀዋለሁ እኔጋ ነው ያለ ስትለው ዘወር ስትል ጊዜ የተንሸራተተብህ መስሎት ከጠላትህ ጋር ይሰለፋል በነገራችን ላይ ብርሀኑ ነጋ ወደ ተቃዋሚነት ጎራ ያመጣው ይህ ባህሪው ነው። መለስ ዜናዊ! በረከትሰመኦን፣ እሰየ አብርሃ ፣ክንፈ ፣ገነተ ዘወዴ፣አባይ ፀሐይ፤ ታምራት ላይኔና ሌሎች ከፍተኛ የሲቤልና የሚሊታሪ ባለሥልጣኖች ወዳጆቹ አጫዋቻቸው ነበር። በምዕራቡ አለም የቀለም ትምህርት ተቀኝንቶ በአራዳ ልጅ ህይወት ያደገው ብርሀኑ ነጋ ከበርህ ለመጡት ትልቅ ሙሁራቸውና አጫዋቻቸው ነበር ለመጠጥና ለመዝናናት ሲወጡ ብርሀኑም ይመጣል ከተባለ የሚቀር የለም። ምርጫ 97 ሲመጣ የተቃማወች ትግል ሲጠነከር የህዋት ወያኔ ዕድሜ ሲጨልም የታየው ብርሀኑ ጓደኞቹን ከዶ ተቃዋሚ ሲሆን ምልክት አላሳያቸውም ይልቁንም ሥርዓቱን በመራገምና በማውገዝ በተደረገው የቴሌብጅን ክርክር ዋነኛ ተዋናይ ሁኗ ቀረበ ሁሉም ወያኔዎች በብርሀኑ ክህደት ገርሟቸዋል እንደ መለስና በረከት ግን የተደነቀ የለም ከምርጫው በኃላ ወያኔ ኢህአዴግ ምርጫ ያልኩት የምእራብያውያን ልብ ለማማለል እንጂ በደም ያመጣሁትን ሥልጣን በምርጫ ካርድ አልሰጥም ብሎ የኃይል እርምጃ ሲወስድ ድምፁን ለማስከበር የተዘጋጀውን የሕዝብ ተቃውሞ ያከሸፈው ዶ/ ር ብርሀኑ ሲሆን ወዲያውኑ ከወያኔዎች ለመለጠፍ ብርቱ ጥረት አድርጓ ሳይሳካለት ቀርቶአል አብረውት የታሰሩትን የቅንጅት አመራሮች በመካድና በመከፋፈል አመራሩን ስም በማጥፋትና በመበከል መሪዎችንና ድርጅቱን ደብዛቸውን ያጠፋው ብርሀኑ ነጋናበርሱ የሚመራው የጋንግ ቡድን ነው። ሌላው ቀርቶ ዶ / ር ብርሀኑ ከእስር ተፈቶ ከወ/ ሮ ብርካን ሚዴቅሳ ጋር በየስቴቲ ጉብኝት ሲዳርጉ ጀምሮ ፕሮሞት ሲዳርጓቸው የነበሩ ና ዶክተር ብርሀኑ ለቀጣይ ፖለቲካው አስተዋጽኦ ያደረጉለት ለእርሱ

ከእስር መፈታት በዲያስፖራና በዲፕሎማሲ ሕዝቡን በማደራጀት ትልቁን ስራ የሠሩት ፖለቲከኞች ፣ ጋዜጠኞች ፣ የድህረ ገፅ አዘጋጆች፣ አክታብስቶች በሙሉ በዶ/ ር ብርሀኑ ተክደዋል ምክንያቱም ከሻቢያ መንግሥት ጋር ባላቸው የአቋም ልዩነት ወያኔ ተብለዋል ። ይህን የወያኔ ሥርዓት ከውልደቱ ጀምረው አምርረው ታግለው ያታገሉ እነ ኢልያስ ክፍሌ ፣ጋዜጠኛ አበበ በለው፣ ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ ወዘተ ብርሃኑ ነጋ በሕዝብ ፊት ቀና ብሎ እንዲሄድ አድርገው ዛሪ ባላቸው ተመክሮ በኤርትራ የማደረገው ትግል አደጋ አለው ኤሲያስ አፈወርቂ ለኢትዮጵያ አንድነት ስጋት ነው በሚለው አመለካከታቸው ሕይወቱን በክህደት የሚመራው ብርሀኑ ነጋና ጭፍን ደጋፊዎቹ ወያኔዎች ናቸው ሲሉ አያፍሩም ለራሳቸው ሞራል አይጨነቁም። ለራሳቸው ክብር ስለማይሰጡ ለሌላው አይጨነቁም ።

ሁለተኛው የብርሃኑ ነጋ ባህራዊ አንደ ሙህር ሳይሆን እነደ ትንሽ ልጅ አትኩሮትን ( attention ) ፈላጊ ነው ። ይህን ካጣ በተቃራኒው ሌላው ከሰጠው በአቋሙ ለመገልበጥና ጓደኞቹንና ወዳጆቹን ለማራገፍ ወደኃላ አይልም ተሞክሮው የሚሳየው ይህን ነው። ዶ/ ር ብርሃኑ አሁን ያለው የፖለቲካ አቋሞቹ በሙሉ ወደኃላ ተሔዶ ቢፈተሽ ፍፅም ተቃራኒ ሁነው እናገኛቸዋለን የዶክተር ብርሃኑ አቋም የሚወሰነው በመርህ ደረጃ ሳይሆን ሊንከባከበው የሚችል ፣ እርሱን ከፊት የሚቆመውና ማይክራፎን የማይነሳው ለማንኛው ኃይል ራሱን ለመሸጥ ያዘጋጀ ግለሰብ ነው። የትኩረት ፈላጊ ጥም ስላለበት የፖሊቲካ ሀሳብ መገለባበጥና መንሸራተት ብቻ ሳይሆን የለሙያዉና ችሎታው ጦር መሪ እስከመሆን ይሄዳል ። የዶ /ር ብርሀኑ ኤርትራ አካሄድ እንደ ትልቅ ጀብድ ሲነገርለት እሰማለሁ ኤርትራ መሄድም የመጀመሪያው ሰው እንደሆነ ከዚህ በፊት የሄዱትንና ያጋጠማቸውን ችግር የተናገሩትን እንደ እርኩስ ሲወገዙ እሰማለሁ ስለጥረታቸው እንኳ አይመሰገኑም ያሳዝናል ። ያም ሆነ ይህ ብርሃኑ ወደ ኤርትራ የሄደበት በሁለት መንገዶች ነው። አንደኛው እስከዛሬ በየመድረኩ በሚካሄደው ፕርፖጋንዳ የኢትዮጵያ ልጆች ፤ የሀገራችን የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል ሰለባ አድርጓቸው ነበር አሁን ግን ለራሱ ፕርፖጋንዳ እሱ ራሱ ዋጋ የሚከፍልበት ጊዜ በመምጣቱ ነው። አሁን

ለጊዜው አስመራ ከተማ በተንጣለለ አፓርትመንት ወጣ እያለ ከነ ሁዳስና ትርሓስ ጋር ከዚህ ከዲያስፖራ በሚላክለት ገንዘብ ከሻቢያ ባለሥልጣናት ዉስካ እየተራጨ ዙ እንደሚጎበኝ አንዳንዴ አሉ የሚባሉትን ወታደሮች እየጎበየ ከአሜሪካ የጭንቀት ኑሮ በተሻለ በደጋፊዎቸም አንቱ ተብሎ ሊኖር ይችላል አንድ ቀን እውነት ይወጣል ።ሁሌ ግን ዋሽተህ መኖር አይቻልም

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።